፲፯፤ ወአምሥጡ፡ ድሙራንኪ፤

ትገዢያቸው፡ የነበሩ፡ እስራ ኤል፡ ሄዱ፤

ከመ፡ አንበጣ፡ ዘይነብር፡ ላዕለ፡ ጥቅም፡ በዕለተ፡ ጊሜ፡ ወቈር፤

በጉም፡ በብርድ፡ ቀን፡ አንበጣ፡ በቅጽር፡ ላይ፡ እንዲሰፍር፤

ወእምከመ፡ ሠረቀ፡ ፀሐይ፡ ይትገኀሡ፡

ፀሐይ፡ በወጣ፡ ጊዜ፡ ተነሥቶ፡ እንዲሄድ፡ ትገዢያቸው፡ የነ በሩ፡ እስራኤል፡ ይሄዳሉ፤

ወኢያእመረት፡ ብሔራ፤

እሷ፡ ግን፡ አገሯን፡ አላወቀች ውም፡ ማለት፡ ለመማረኳ፡ መመ ለስ፡ የለውም፤

፲፰፤ አሌ፡ ሎሙ፡ እስመ፡ ደቀሱ፡ ኖሎትኪ፤

ነገሥታቱ፡ የሞት፡ እንቅልፍ፡ አንቀላፍተዋልና፡ ወዮላቸው፤

ንጉሠ፡ ፋርስ፡ አኖሞሙ፡ ለኃያላንኪ፤

አርበኞችሽን፡ ቂሮስ፡ የሞት፡ እን ቅልፍ፡ እንዲያንቀላፉ፡ አድር ጓቸዋልና፤

ወግዕዙ፡ አሕዛብኪ፡ ውስተ፡ አድባር፤

ሠራዊቶችሽ፡ ወደአምባው፡ ሸሹ፤

ወአልቦ፡ ዘይሬኢ

የሚያይሽ፡ የለም፤

ወአልቦ፡ ዘይጸንዕ፤

አንቺን፡ ደጅ፡ የሚጠናሽ፡ የለም፤

፲፱፤ ወአልቦ፡ ፈውስ፡ ለቍስልኪ፤

ለቁስለ፡ መከራሽ፡ ድኅነት፡ የለውም፤

ኵሕሰ፡ ፀልዕኪ፤

ቁስለ፡ መከራሽ፡ ሰፋ፤ ይህንን፡ ናሆም፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ባንቺ፡ ጠፋልን፡ ሲል፡ ፈዋሲተ፡ ቍስሉ፡ ለናሆም፡ ብሎ፡ አባ፡ ሕርያ ቆስ፡ ወስዶታል፤

ወኵሎሙ፡ እለ፡ ሰምዑ፡ ዜናኪ፡ ይጠፍሑ፡ እደዊሆሙ፡ ላዕሌኪ፤

ያንቺን፡ ወሬ፡ የሚሰሙ፡ ሁሉ፡ እጃቸውን፡ ያጨበጭባሉ፤

እስመ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ በጽሐ፡ እከይኪ፡ በኵሉ፡ ጊዜ፤

ክፋትሽ፡ በየጊዜው፡ በሁሉ፡ ላይ፡ ደርሷልና፤

ተፈጸመ፡ ዘናሆም፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ የሃሉ፡ ምስሌነ፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፤

አነሣሥቶ፡ ለአስጀመረን፡ አስ ጀምሮ፡ ለአስፈጸመን፡ ለእግዚ አብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግ ባው፡ አሜን፡ በውነት።

# ዘዕንባቆም፡ ነቢይ

## መቅድም

ዕንባቆም፡ ማለት፡ ማእምር፤ ለባዊ፤ ነባቢ፡ ማለት፡ ነው፤ ይኸም፡ ዕንባቆም፡ አዝመራውን፡ ለሚያጭዱ፡ ምሳ፡ ይዞ፡ ሲሄድ፡ መልአኩ፡ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ሰድ፡ ዘንተ፡ ምሳሐ፡ ለዳንኤል፡ እትከ፡ ዘሀሎ፡ ውስተ፡ ግበ፡ ባቢሎን፡ አለው፤ ይኸንን፡ የያ ዘኸውን፡ ምሳ፡ በአናብስት፡ ጉድጓድ፡ ላለ፡ ለወንድምህ፡ ለዳ ንኤል፡ ውሰድለት፡ አለው፤ ዕን ባቆምም፡ ባቢሎንሃ፡ ኢየአምር፤ ባቢሎንን፡ አላውቃትም፤ ግበ፡ አናብስትሂ፡ ኢርኢኩ፤ የአናብ ስትንም፡ ጉድጓድ፡ አላየሁም፡ አለው፤ መልአኩ፡ በራሱ፡ ላይ፡ ተሸክሞ፡ ወስዶ፤ አንድም፡ በአ ንዲት፡ ጠጕሩ፡ አንጠልጥሎ፡ ወስዶ፡ በባቢሎን፡ ጣለው፤ የአ ንበሳው፡ ጉድጓድ፡ እንደተዘጋ፡ ገብቶ፡ ለዳንኤል፡ ምግቡን፡ ሰጥቶት፡ ሄዷል፤

ዳንኤልም፡ ተዘከረኒኑ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኢኃደጎሙ፡ ለእለ፡ ያፈቅርዎ፤

ትንኚን፡ በምግብ፡ የሚያስብ፡ እግዚአብሔር፡ አሰበኝ? ብሎ፡ አድንቋል፤ ይኸውም፡ ለጊ ዜው፡ ተደርጓል፡ ለኋላው፡ [illegible] አናብስት፡ [illegible] ምግቡ፡ የም

ግበ፡ ነፍስ፤ እንባቆም፡ የጌታ፡ ምሳሌ፡ ነው፤ እንደተዘጋ፡ ገብቶ፡ እንደተዘጋ፡ መውጣቱ፡ ጌታ፡ በኅቱም፡ ድንግልና፡ ተፀንሶ፡ በኅ ቱም፡ ድንግልና፡ ለመወለዱ፡ ምሳሌ፡ ነው፤ ዳግመኛ፡ አራቱ፡ ነገሥተ፡ ፍልስጥኤምን፡ ይዞ፡ አምስቱ፡ ነገሥተ፡ ምድያምን፡ ድል፡ ነስቷል፤ በዔዋዌም፡ ጊዜ፡ ፍልስጥኤም፡ ከምትባል፡ አምባ፡ ገብቶ፡ ድኗል፤ ትውልዱ፡ ነገዱ፡ ከነገደ፡ ስምዖን፡ ነው፤ አባቱ፡ ዳኮር፡ እናቱ፡ ሬፋ፡ ይባላሉ፤ መነሣቱ፡ በሕዝቅያስ፡ ዘመን፡ ነው፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ተረፈ፡ ዘርአየ፡ ዕንባቆም፡ ነቢይ፤

ናሆም፡ ከማየት፡ የቀረው፡ ዕን ባቆም፡ አይቶ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ አንድም፡ ጌታ፡ በእ ስራኤል፡ ከማናገር፡ የቀረው፡ ዕንባቆም፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤

፪፤ እስከ፡ ማዕዜኑ፡ እግዚኦ፡ ንኬ ልሁ፡ ኀቤከ፡ ወኢትሰምዓነ፤

አቤቱ፡ እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ እንጮሃለን? አንተስ፡ ምነው፡ አትሰማን?

www.ethiopianorthodox.org

ነአወዩ፡ ኀቤከ፡ ተገፊአነ፡ ወኢታድኅነነ፡ እንከ፤

ተበድለን፡ ወደአንተ፡ እንጮሃ ለን፡ ምነው፡ አታድነን፤

፫፤ ወለምንት፡ አርአይከኒ፡ ፍትሐ፡ ከመ፡ እርአይ፡ ኃሣረ፡ ወሕማመ፤

ያሥሩን፡ ነገድ፡ የሁለቱን፡ ነገድ፡ መከራቸውን፡ አይ፡ ዘንድ፡ እን ዲህ፡ ያለ፡ ፍርድ፡ ለምን፡ አሳየኸኝ?

በቅድሜየ፡ ኮነ፡ ፍትሕ፡ ግፍቱዕ፤

በፊቴ፡ ግልብጥብጥ፡ ያለ፡ ፍርድ፡ ተፈረደ፤

ወመኰንንኒ፡ ይትኄለይ፡ ኅልያነ፤

ግልብጥብጥ፡ ያለ፡ ፍርድ፡ ይህ፡ ነው፤ ዳኛው፡ መማለጃ፡ ተቀ ብሎ፡ ይፈርዳል፤

፬፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ዓለዉ፡ ሕገከ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ሕግህን፡ አፈረሱ፤

ወኢይወጽእ፡ ፍትሐ፡ ጽድቅ፤

እውነት፡ ፍርድ፡ አይፈረድም፤

እስመ፡ ኃጥዕ፡ ይትዔገሎ፡ ለጻድቅ፤

አሕዛብ፡ እስራኤልን፡ ይቀሟ ቸዋልና፤ አንድም፡ ባለጸጎች፡ እስራኤል፡ ድሆች፡ እስራኤ ልን፡ ይቀሟቸዋልና፤

በእንተ፡ ዝንቱ፡ ይወጽእ፡ ፍትሕ፡ ግፍቱዕ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ግልብጥብጥ፡ ያለ፡ ፍርድ፡ ይፈረዳል፤

፭፤ ርእዩኬ፡ እለ፡ ታስተሐቅሩ፤

ዔዋዌ፡ አለ፡ ቢሏችሁ፡ የለም፡ በማለት፡ የምትንቁ፡ የምታቃ ልሉ፡ እዩ፤

ወነጽሩ፤

አስተውሉ፤

ወአንክሩ፡ መንክረ፡

እመኑ፤

ወትማስኑ፤

አናምንም፡ ብትሉ፡ ግን፡ ትጠ ፋላችሁ፤

እስመ፡ ግብረ፡ እገብር፡ አነ፡ በመዋዕ ሊክሙ፡ ዘኢተአምሩ፡ አንትሙ፤

እናንተ፡ የማታውቁትን፡ ዔዋ ዌን፡ በዘመናችሁ፡ አደርጋለሁና፤

ወእመሂ፡ ነገሩክሙ፤

ዔዋዌ፡ አለ፡ ብለው፡ ቢነግሯ ችሁ፡ የምትንቁ፤ የምታቃልሉ፡ እናንተ፡ ትጠፋላችሁ፤ አንድም፡ ርእዩ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ሚጠት፡ አለ፡ ቢሏችሁ፡ የለም፡ በማ ለት፡ የምትንቁ፤ የምታቃልሉ፡ እዩ፤ ወነጽሩ፤ አስተውሉ፤ ወአንክሩ፤

እመኑ፤ አናምንም፡ ብትሉ፡ ግን፡ ትጠፋላችሁ፤ ሚጠት፡ አለ፡ ብለው፡ ቢነግሯችሁ፡ የም ትንቁ፤ የምታቃልሉ፡ የማታ ውቋትን፡ ሚጠትን፡ በዘመና ችሁ፡ አደርጋለሁና፤



ሥጋዌ፡ አለ፡ ቢሏችሁ፡ የለም፡ በማለት፡ የምትንቁ፤ የምታቃ ልሉ፡ እዩ፤ አስተውሉ፤ እመኑ፤ አናምንም፡ ብትሉ፡ ግን፡ ትጠ ፋላችሁ፤ በዘመናችሁ፡ ሥጋ ዌን፡ አደርጋለሁና፡ ሥጋዌ፡ አለ፡ ብለው፡ ቢነግሯችሁ፡ የለም፡ በማለት፡ የምትንቁ፤ የምታቃልሉ፤ እመኑ፤ አናም ንም፡ ብትሉ፡ ግን፡ ትጠፋላችሁ፤

፮፤ ወናሁ፡ አነ፡ እፌኑ፡ ላዕሌክሙ፡ ፋርስሃ፡ መስተቃትላነ፤

አርበኞች፡ የሆኑ፡ የፋርስን፡ ሰዎች፡ አመጣባችኋለሁ፤

ወሕዝበ፡ መሪራነ፤

ቁጡ፡ የሆኑ፡ ወገኖችን፡ አመ ጣባችኋለሁ፤

ወረዋፅያነ፡ እለ፡ የሐውሩ፡ በስፍሐ፡ ምድር፤

በምድር፡ መልተው፡ የሚሔዱ፡ ፈጣኖች፡ የሆኑ፡ የፋርስ፡ ሰዎ ችን፡ አመጣባችኋለሁ፤

ከመ፡ ይረሱ፡ አብያተ፡ ዘኢኮነ፡ ዚአሆሙ፤

ገንዘባቸው፡ ያይደለ፡ የእስራኤ ልን፡ ቤት፡ ይወርሱ፡ ዘንድ፤

፯፤ ግሩም፡ ራእዩ፤

የስልምናሶር፡ መልኩ፡ ልዩ፡ ነው፤ ያስፈራል፤ አንድም፡ መልክዓ፡ ፍትሑ፡ ልዩ፡ ነው፤

ወእምውስቴቱ፡ ይከውን፡ ፍትሑ፤

ፍርዱ፡ ከሱ፡ ይገኛል፤

ወተረፋሂ፡ እምኔሁ፡ ይወጽእ፤

ይግባኙ፡ ከሱ፡ ነው፤ አንድም፡ ግሩም፡ ራእዩ፡ ብለህ፡ መልስ፤ የናቡከደነፆር፡ መልኩ፡ ልዩ፡ ነው፤ አንድም፡ መልክዓ፡ ፍትሑ፡ ልዩ ነው፤ ፍርዱ፡ ከሱ፡ ይገ ኛል፤ ይግባኙ፡ ከሱ፡ ነው፤ አን ድም፡ የሰናክሬም፡ መልኩ፡ ልዩ፡ ነው፡ ያስፈራል፤ አን ድም፡ መልክአ፡ ፍትሑ፡ ልዩ፡ ነው፤ ፍርዱ፡ ከሱ፡ ይገኛል፡ ይግባኙ፡ ከሱ፡ ነው፤ አንድም፡ የጌታ፡ መልኩ፡ ልዩ፡ ነው፤ ይሜኒ፡ ላህዩ፡ ይለዋልና፡ ፍርዱ፡ ከሱ፡ ይገኛል፤ ተኃ ድግ፡ ለኪ፡ ኃጢአትኪ፡ እያለ፡ ይፈርዳል፤ ወተረፋሂ፡ ንዑና፡ ሐሩ፡ ከሱ፡ ይገኛል፤

፰፤ ይወጽኡ፡ ወይሠርሩ፡ ከመ፡ ነምር፡ አፍራሲሆሙ፤

ፈረሶቻቸው፡ እንደነብር፡ ፈጣኖች፡ ናቸው፤

ወይበድሩ፡ እምተኵላተ፡ ዓረብ፤

በምዕራብ፡ እኩል፡ ካሉ፡ ተኩ ላዎች፡ ይቀድማሉ፤ በአንዱ፡ መዓዝኑን፡ ሁሉ፡ መናገር፡ ነው፤ ከዋክብተ፡ ጽባሕ፡ አናብስተ፡ መስዕ፡ ይላል፤ በሌላው፡ የሌ ሉ፡ ሁነው፡ ነውን፡ በዝተው፡ በሚገኙበት፡ መናገር፡ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይሠርሩ፡ ከመ፡ ንስር፡ ዘይጋጉዕ፡ ለበሊዕ፤

ለመብላት፡ እንደሚቸኩል፡ አሞራ፡ ፈጣኖች፡ ናቸው፤

ወይበጽሑ፡ እምርኁቅ፡ አፍራሲሆሙ፤

ፈረሶቻቸው፡ ከሩቅ፡ ናቸው፡ ሲሿቸው፡ ፈጥነው፡ ይደርሳሉ፤

፱፤ ወይበጽሖሙ፡ ጥፍዓት፡ ለኃጥአን፡ እለ፡ ይትቃወሙ፡ ፍጽመ፡ ቅድመ፡ ገጾሙ፤

ሕግን፡ ፊት፡ ለፊት፡ በሚቃወሙ፡ በኃጥአን፡ ጥፋት፡ ይመጣባቸዋል፤

ወያስተጋብዑ፡ ፄዋሆሙ፡ ከመ፡ ሆፃ፡ ባሕር፤

ምርኳቸውን፡ እንደ፡ ባሕር፡ አሸዋ፡ አብዝተው፡ ይሰበስባሉ፤

፲፤ ወውእቱ፡ ይነግሥ፡ ቦሙ፤

ስልምናሶር፡ ናቡከደነፆር፡ ይነግሥባቸዋል፤ አንድም፡ ሎሙ፡ ይላል፤ በስልምናሶር፡ ሰናክሬም፤ በናቡከደነፆር፡ ብልጣሶር፡ ነግሦባቸዋል፤

ወይትፌጋዕ፡ በላዕሌሆሙ፤

በነዚያ፡ ላይ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ያደርጋል፤

ወኃያላን፡ ተውኔቱ፤

የእስራኤል፡ አርበኞች፡ መጫወቻው፡ ናቸው፤

ወይሤለቅ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ አዕዋኒሆሙ፤

በአምባቸው፡ ሁሉ፡ ይዘብታል፤ ጽኑ፡ አምባ፡ ነው፤ የሚባል፡ ይህ፡ ነው? እያለ፤ አንድም፡ በአርበኞቻቸው፡ ላይ፡ ይዘብታል፤ ኃያላን፡ ናቸው፡ የሚባሉ፡ እሊህ፡ ናቸው? እያለ፤

ወይደፍኖሙ፡ በመሬት፤

በጉድጓድ፡ ይቀብራቸዋል፤

ወትእኅዞሙ፡ እኪት፤

እነሰናክሬምን፡ መከራ፡ ታገኛቸዋለች፤

፲፩፤ ወእምዝ፡ ይመይጥ፡ መንፈሶ፤

ሰናክሬም፡ ልቡናውን፡ ቦኑ፡ ግልፎ፡ ወደማለት፡ ይመልሳል፤ አንድም፡ ቦኑ፡ ግልፎ፡ ካለ፡ በኋላ፡ ሰውነቱ፡ ወደሀገሩ፡ ይመለሳል፤

ወይሰምዕ፡ ድምፀ፤

አጋንንት፡ የመብረቅ፡ ድምፅ፡ ያሰሙታል፤

ወየሐልፍ፡ ወይትመየጥ፤

ሰባት፡ ፈረሰኛ፡ አሥራ፡ አምስት፡ እግረኛ፡ ሆኖ፡ ይሄዳል፤

ወኢያመስጥ፡ ዛቲ፡ ኃይሉ፡ ለአምላኪየ፤

ከእደ፡ እግዚአብሔር፡ አያመልጥም፤ ከቤተ፡ ጣዖት፡ ገብቶ፡ ሲሰግድ፡ [illegible]



ሰዓት፡ በሙቀጫ፡ ዘካዘና፡ ቀጥቅጠው፡ ገድለውታልና፤ አንድም፡ ወይመይጥ፡ መንፈሶ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ናቡከደነፆር፡ ልቡናውን፤ አነ፡ ውእቱ፡ ዘአሠርቅ፡ ፀሐየ፤ ወደማለት፡ ይመልሰዋል፤ ኃለፈት፡ መንግሥትከ፤ የሚል፡ ድምፅ፡ ይሰማል፡ አራዊት፡ ሆኖ፡ ወደምድረ፡ በዳ፡ ይሄዳል፤

ወኢያመስጥ፤

ከእደ፡ እግዚአብሔር፡ አያመልጥም፤ ኃማው፡ ተመልጧል፤ ጥፍሩ፡ ተልጧልና፤ አንድም፡ ወእምዝ፡ ይመይጥ፡ ብልጣሶር፡ በዓህሉ፡ ፊትፍታችሁ፡ አብሉበት፤ በጽዋው፡ ቀድታችሁ፡ አጠጡበት፡ ወደማለት፡ ልቡናውን፡ ይመልሳል፤ ወይሰምዕ፡ ድምፀ፤ ማኔ፡ ቴቄል፡ የሚል፡ ድምፅ፡ ይሰማል፤ ወየኃልፍ፡ ይሞታል፤ አንድም፡ ብልጣሶር፡ በዓህሉ፡ ፊትፍታችሁ፡ አብሉበት፤ በጽዋው፡ ቀድታችሁ፡ አጠጡበት፡ ካለ፡ በኋላ፡ ሰውነቱ፡ ወደሀገሩ፡ ይመለሳል፤ ወይሰምዕ፡ ነቢዩ፡ ማኔ፡ ቴቄል፡ ፋሬስ፡ ብሎ፡ ሲተረጕ[illegible] ልፍ፡

ወደ፡ ፍርሃት፡ ወደ፡ ድንጋጤ፡ ይሄዳል፤ ወኢያመስጥ፡ ከእደ፡ እግዚአብሔር፡ አያመልጥም፤ የፈረስ፡ መጨኼው፡ ገድሎታልና፤ አንድም፡ ወእምዝ፡ ዲያብሎስ፡ ከተፈጠረ፡ በኋላ፡ አነ፡ ፈጣሪሆሙ፡ ወደ፡ ማለት፡ ይመለሳል፤ ወይሰምዕ፡ ለይኩን፡ ብርሃን፡ ሲል፡ ይሰማል፤ ወየኃልፍ፡ ወደ፡ እንጦርጦስ፡ ይወርዳል፤ ወኢያመስጥ፤ ከእደ፡ እግዚአብሔር፡ አያመልጥም፤ ብርሃኑን፡ ገፍፎ፤ ጨለማ፡ አጐናጽፎ፡ አውርዶታልና፤ ዛቲ፡ ኃይሉ፡ ለአምላኪየ፤ የፈጣሪዬ፡ ኃይሉ፡ ይህች፡ ማጥፋት፡ ናት፤

፲፪፤ አኮኑ፡ አንተ፡ አቅደምከ፡ እግዚኦ፡ አምላኪየ፡ ቅዱስ፡ ዘኢትመውት፤

የማትሞት፡ ጽኑ፡ ክቡር፡ የምትሆን፡ ፈጣሪዬ፡ አስቀድመህ፡ አሰናብተኸኝ፡ የለም?

እግዚኦ፡ ለኮነኔ፡ ሠራዕካሁ፤

አቤቱ፡ ሕግን፡ ለመከራ፡ የሠራኸው፡ አይደለም?

ወፈነውከኒ፡ ከመ፡ እዝልፍ፡ በተግሣጽ፤

በሕግ፡ ጸንቼ፡ አስተምር፡ ዘንድ፡ የሰደድኸኝ፡ አይደለም?

www.ethiopianorthodox.org

፲፫ ፤ ኦ፡ ንጹሐ፡ ዓይን፡ እምነ፡ እኩይ፤ ኢትኔጽርኑ፡ ዘንተ፡ እኩየ፡ ሕማመ፡ ወጻዕረ፤

ክፉን፡ ነገር፡ ከማየት፡ ንጹሐ፡ ሕሊና፡ የምትሆን፡ ይህን፡ ክፉ ውን፡ ነገር፡ መከራውን፤ ፃሩን፤ ጋሩን፡ አታይም? ኦ፡ ንጹሐ፡ ሕሊና፡ እምነ፡ አሕስሞ፡ ይላል፤

ለምንትኑ፡ እንከ፡ ታሬምም፡ እንዘ፡ ትሬእዮሙ፡ ለእለ፡ ያስተአክዩ፤

ሕግ፡ እግዚአብሔርን፡ የሚንቁ፤ የሚያቃልሉ፡ ሰዎችን፡ እያ የህ፡ ለምን፡ ዝም፡ ትላለህ?

ወይውኅጦ፡ ኃጥእ፡ ለጻድቅ፤

አሕዛብ፡ እስራኤልን፤ አንድም፡ ባለጸጎች፡ እስራኤል፡ ድሆች፡ እስራኤልን፡ እንደ፡ ዕንቀት፡ ሲጠጧቸው፤ እንደ፡ ጥህሎ፡ ሲውጧቸው፡ ለምን፡ ዝም፡ ትላለህ?

፲፬ ፤ ወትሬስዮሙ፡ ለሰብእ፡ ከመ፡ ዓሣተ፡ ባሕር፤

ሰዎችን፡ እንደ፡ ባሕር፡ ዓሣ፡ ለምን፡ ታደርጋቸዋለህ? ግፍስ፡ በባሕር፡ ይመሳ፤ ዓሣውን፡ ዓሣ፡ ይበላ፡ እንዲሉ፤

ወከመ፡ አርዌ፡ ዘአልቦ፡ መኰንን፤

ገዥ፡ እንደሌለው፡ እንደ፡ ጅብ፡ ለምን፡ ታደርጋቸዋለህ?

፲፭ ፤ በመሥገርቱ፡ አውጽአ፡ ያህልቆ፤

በኃጢአቱ፤ አንድም፡ በምክሩ፤ አንድም፡ በሠራዊቱ፡ ጣዖቱን፡ አመጣ፤

ወሰሐቦ፡ በመርበብቱ፤

በኃጢአቱ፤ አንድም፡ በምክሩ፤ አንድም፡ በሠራዊቱ፤

ወአስተጋብአ፡ በመሥገርቱ፤

በኃጢአቱ፡ በምክሩ፡ በጣዖቱ፡ ሰበሰባቸው፤

በእንተ፡ ዝንቱ፡ ይትፌሣሕ፡ ወይትሐሠይ፡ ልቡ፤

ፈቃዱ፡ ስለተፈጸመ፡ ልቡናው፡ ደስ፡ ይለዋል፤

፲፮ ፤ ወይሠውዕ፡ ለመሥገርቱ፤

ለሠራዊቱ፡ ፍሪዳ፡ ያርዳል፤ አንድም፡ ለጣዖቱ፡ መሥዋዕ ት፡ ይሠዋል፤

ወየዓጥን፡ ለመርበብቱ፤

ሠራዊቱን፡ ሽቱ፡ ይቀባቸዋል፤ አንድም፡ ለጣዖቱ፡ ዕጣን፡ ያጥናል፤

እስመ፡ በሙ፡ አስብሐ፡ መክፈልቶ፤

እድል፡ ፈንታውን፡ በነዚህ፡ ያበዛሁ፡ ይመስለዋልና፤

ወኅሩየ፡ ረሰየ፡ ሲሳዮ፤

ምግቡን: ...



፲፯ ፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ይሬብብ፡ መሥገርቶ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ኃጢአቱን፡ ይሠ ራል፤ ጣዖቱን፡ ያመልካል፤

ወዘልፈ፡ ይቀትሎሙ፡ ለአሕዛብ፡ ወኢይምሕኮሙ፤

አሕዛብን፡ ያጠፋቸዋል፤ አይ ራራላቸውም።

## ምዕራፍ ፪

፩ ፤ ወአነ፡ እቀውም፡ ዲበ፡ መዓቅብ፤

በረድኤተ፡ እግዚአብሔር፡ ተጠ ብቄ፡ እኖራለሁ፤

ወዓዐርግ፡ ዲበ፡ ኰኵሕ፤

ወደፍልስጥኤም፡ እወጣለሁ፤

ወአፀምዕ፡ በአእምሮ፡ ዘይነብበኒ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ የሚነግረኝን፡ ነገር፡ በአእምሮ፡ አዳምጣለሁ፤ በተማላ፡ መስማት፡ እሰና፤ አንድም፡ እግዚአብሔር፡ የሚ ነግረኝን እውቀትን አደምጣለሁ፤

ወአወሥኦ፡ ለዘይዛለፈኒ፤

ለሚነግረኝ፡ እመልስለታለሁ፤

፪ ፤ ወተሰጥወኒ፡ እግዚአብሔር፡ ወይቤለኒ፡ ጸሐፍ፡ ነገረ፡ ራእይ፡ ዘይ ከውን፡ በዕድሜሁ፡ ውስተ፡ ሰሌዳ፡ ከመ፡ ያፍጥን፡ ዘያነብቦ፤

እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለኝ፤ መለሰልኝ፤ የሚያነበው፡ ሰው፡ ፈጥኖ፡ ያነበው፡ ዘንድ፡ በጊ ... ራእ

ዩን፡ ነገር፡ በብራና፡ አጉል ተህ፡ ጻፍ፡ አለኝ፤

እስመ፡ ዓዲሁ፡ ሀለወ፡ ራእይ፡ በዕድሜሁ፤

ዳግመኛ፡ ራእዩ፡ በጊዜው፡ ጊዜ፡ ይደረጋልና፤

ወይሠርቅ፡ በማዕዶቱ፤

በራእዩ፡ አንፃር፡ ዔዋዌ፤ በዔ ዋዌ፡ አንፃር፡ ሚጠት፡ ይደ ረጋልና፤

፫ ፤ ወአኮ፡ ለከንቱ፤

ሳይደረግ፡ የሚቀር፡ አይደለም፤

እመሂ፡ ጐንደየ፡ ጽንሖ፡ እስከ፡ ይበጽሕ፤

ቢዘገይም፡ ጊዜው፡ እስኪደርስ፡ ደርሰህ፡ ጠብቀው፤

ወኢይጐነዲ፤

ሚጠት፡ ሥጋዌ፡ አይቀርም፤

፬ ፤ ወእመሰ፡ ተመይጠ፡ ኢትሠ ምር፡ ቦቱ፡ ነፍስየ፤

ሰናክሬም፡ ቦኑ፡ ግልፎ፡ ወደ ማለት፡ ቢመለስ፡ ልቡናዬን፡ ደስ፡ አይላትም፤ አንድም፡ ብል ጣሶር፡ በጻሕሉ፡ ፈትፍታችሁ፡ አብሉበት፤ በፅዋው፡ ቀድታ ችሁ፡ አጠጡበት፡ ወደማለት፡ ቢመለስ፡ ልቡናዬን፡ ደስ፡ አይላትም፤

ጻድቅሰ፡ በአሚን፡ የሐዩ፤

ሕዝቅያስ፡ ዘሩባቤል፡ ግን፡ በሃ ይማኖት፡ጸንቶ፡ ይኖራል፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም፡ ጻድቅ፡ ሰው፡ በሃይ ማኖት፡ ጸንቶ፡ ይኖራል፤

፭፤ ወብእሲስ፡ ነባቢ፡ ወመስተ ሐቅር፡ ኢየመሥጥ፡ በምንትኒ፤

ሰውን፡ የሚንቅ፡ የሚያቃልል፡ ቀባጣሪ፡ ሰው፡ ግን፡ ከመከራ፡ አይድንም፤

በከመ፡ አርኀበ፡ ነፍሶ፡ ሲኦል፡ ወኢ ይፀግብ፡ ሞት፤

ሞት፡ ቢገድል፡ ቢገድል፡ መቃ ብር፡ ቢቀበል፡ ቢቀበል፡ በቃኝ፡ እንዳይል፤ ስልምናሶር፡ ቢማ ርክ፡ ቢማርክ፡ በቃኝ፡ አይልም፤

ወያስተጋብዕ፡ ኀቤሁ፡ ኵሎ፡ አሕዛበ፤

ሰውን፡ ሁሉ፡ ወደሱ፡ ይሰበስባል፤

ወይትዌከፎሙ፡ ለኵሎሙ፡ አሕዛብ፤

ቢመለሱ፡ ግን፡ በረድኤት፡ ይቀ በላቸዋል፤

፮፤ ዘንተ፡ ኵሎ፡ ምሳሌ፡ ይሜ ስሉ፡ ላዕሌሁ፤

መቃብር፡ ሞት፡ በሱ፡ ይመ ስሉበታል፤

ወይትናገሩ፡ ምስሌሁ፤

ሞት፡ መቃብር፡ ምሳሌው፡ እን ደሆኑ፡ ይናገራሉ፤

ወይብሉ፡ አሌ፡ሎቱ፡ ለዘያስተጋብዕ፡ ዘኢኮነ፡ ዘዚአሁ፤

ገንዘቡ፡ ያይደለ፡ የሌላውን፡ ገን ዘብ፡ ለሚሰበስብ፡ ወዮለት፤

፯፤ እስከ፡ ምንትኑ፡ ታከብድ፡ ላዕ ሌሆሙ፡ ጋጋ፡ ዓቢየ፤

እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ አገዛዝ፡ ታጸናባቸዋለህ፤

እስመ፡ ግብተ፡ ይትነሣእ፡ ሞት፡ ላዕሌከ፤

ድንገት፡ ሞት፡ ይመጣብሃልና፤

ወይነሥእከ፤

ግድ፡ ይወስድሃል፤

ወይተግሁ፡ መማክርቲከ፤

መካሮችህ፡ በአንተ፡ መከራ፡ ለማምጣት፡ ይተጋሉ፤ ልጆቹ፡ ሰናክሬምን፡ ገድለውታልና፤ አን ድም፡ ብልጣሶርን፡ ቂሮስ፡ ዳርዮስ፡ ገድለውታልና፤

ወትከውኖሙ፡ አንተ፡ ኀብልያ፤

አንተን፡ ይበዘብዙሃል፤

፰፤ ወያሀበልዩከ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ተርፉ፡ አሕዛብ፤

ከሞት፡ የቀሩ፡ አሕዛብ፡ ሁሉ፡ ይበዘብዙሃል፤

እስመ፡ አንተ፡ ሀብለይከ፡ ብዙኃነ፡ አሕዛበ፡ በእንተ፡ ደመ፡ ሰብእ፤

የሰውን፡ ደም፡ ስለማፍሰስ፡ አንተ፡ ብዙ፡ አሕዛብን፡ በዝ ብዘሃልና፤

ወበእንተ፡ ዓመፃ፡ አህጉር፡ ወበሐውርት፤

አገሩን፡ አውራጃውን፡ ሁሉ፡ ስላጠፋህ፤

ወበእንተ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ውስቴታ፤

በሀገሩ፡ ውስጥ፡ ያሉትን፡ ሰዎች፡ ስላጠፋህ፡ ይበዘብዙሃል፤



፱፤ አሌሎ፡ ለዘይትዔገል፡ ትዕ ግልተ፡ እኩየ፡ ለቤቱ፤

ቤቱን፡ አቀናለሁ፡ ብሎ፤ አን ድም፡ ቤቱን፡ ያቀናሁ፡ መስሎት፡ ቅሚያን፡ ለሚቀማ፡ ሰው፡ ወዮለት፤

ከመ፡ ያሥርር፡ ውስተ፡ አርያም፡ ዕጉሊሁ፤

ልጆቹን፡ በልዕልና፡ ያኖር፡ ዘንድ፤

ከመ፡ ይባዕ፡ እምእደ፡ እኩያን፤

ከክፉ፡ ሰዎች፡ እጅም፡ ይድን፡ ዘንድ፡ ብታሠር፡ እፈታበታ ለሁ፡ ይላልና፤

፲፤ ወመከርከ፡ ሐሣረ፡ ለቤትከ፤

ለወገንህ፡ ክፉ፡ ነገር፡ መከርህ፤

ወተአደውከ፡ ብዙኃነ፡ አሕዛበ፤

ብዙ፡ አሕዛብን፡ አጠፋህ፤

፲፩፤ወዐመፀት፡ ነፍስከ፤

ልቡናህ፡ ካደች፤

እስመ፡ ዕብንኒ፡ ተሐውከ፡ እምውስተ፡ ዓረፍት፡ ወጽአ፡ ሦከ፡ ቦቱ፤

ቅጽሩ፡ ፈርሷልና፡ እሾህ፡ ወጣ በት፡ ማለት፡ አርበኛው፡ ጠፍ ቷልና፡ ጠላት፡ ሠለጠነበት፤

## ጉባዔ

፲፪፤ አሌሎ፡ ለዘየሐንፅ፡ አህጉረ፡ በደም፤

የሰውን፡ ደም፡ እያፈሰሰ፡ አገ ሩን፡ አቀናለሁ፡ የሚል፡ ወዮ [illegible]

ወያጸንዕ፡ አህጉረ፡ በዓመፃ፤

አገሩን፡ በግፍ፡ አጸናለሁ፡ የሚል፡ ወዮለት፤

፲፫፤ ኢኮነኬ፡ ዝንቱ፡ እምኀበ፡ እግ ዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ ከሚገዛ፡ ከእግዚአብ ሔር፡ ዘንድ፡ ይህ፡ የታዘዘ፡ አይደለም፤

ወሐልቁ፡ ብዙኃን፡ አሕዛብ፡ በእሳት፤

ብዙ፡ አሕዛብ፡ በእሳተ፡ መዓቱ፡ ጠፉ፤

ወተመንደቡ፡ ብዙኃን፡ ሕዝብ፤

ብዙ፡ ወገኖች፡ በመከራ፡ ተጨነቁ፤

፲፬፤ እስመ፡ መልዐ፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ አዕምሮ፡ ስብሐተ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ማይ፡ ዘይደፍን፡ ባሕረ፤

ውሀ፡ በጉድጓድ፡ እንዲመላ፡ የእግዚአብሔርን፡ ክብር፡ ምስ ጋና፡ ማወቅ፡ በሁሉ፡ ተመል ቷልና፤

፲፭፤ አሌሎ፡ ለዘያስትዮ፡ ለቢጹ፡ በዘይመውት፤

በሚሞት፡ ገንዘብ፡ ባልንጀራ ውን፡ አብዝቶ፡ ለሚያጠጣው፡ ወዮለት፤

ወያሰክሮ፡ በዘየኃሥሮ፤

በሚያዋርደው፡ ገንዘብ፡ እስ ኪሰክር፡ ለሚያጠጣው፡ ወዮለት፤

www.ethiopianorthodox.org

ከመ: ይነጽር: ውስተ: በዓታተ: ምሕራሞሙ፣

የመስገጃቸውን: ዋሻ: ይመለከት: ዘንድ፤

፲፮፤ እስመ: ታስቲ: ኃሣረ: ለክብርከ: ወታረዊ፣

ሃይማኖትን: ለማጥፋት: አብዝተህ: ታጠጣዋለህና፤

ወአንተኒ: ልብ: ረዓድ: ወአንቀልቅል፣

እንዲህ: የምታደርግ: ልቡና: ሆይ: ተንቀጥቀጥ፤

እስመ: አስተየከ: ጽዋዓ: መዓት: እደ: የማኑ: ለእግዚአብሔር፣

የእግዚአብሔር: ሥልጣኑ: ጽዋዓ: መዓቱን: አጠጥቶሃልና፤

ወታገብእ: ኃሣረ: ላዕለ: ክብርከ፣

ክብርህን: ወደተዋርዶ: ትመልሰዋለህ፤

፲፯፤ እስመ: ይደፍነከ: ርኵሰ: ሊባኖስ፣

የአሕዛብ፡ጕስቍልና: ሸፍኖሃልና፤

ወኀርትምና: አርዌ: ገዳም: ያደንግፀከ፣

ፈናፍንታም: ጅብ: ያስደነግጥሃል፤

በእንተ: ደመ: ሰብእ፣

የሰውን: ደም: ስለአፈሰስህ፤

ወኃጢአተ: ብሔር: ወአህጉር፣

በየሀገሩ: በየመንደሩ: ኃጢአት: ስለሠራህ፤

ወኵሎሙ: እለ: ይነብሩ: ውስቴታ፣

በሷ: የሚኖሩ: ሰዎች: ሁሉ: ኃጢአት: ስለሠሩ፤

፲፰፤ ምንተ: እንከ: ይበቍዕ: ግልፎ: ዘገለፉ፣

የቀረጹት: ጣዖት: ምን: ይረባል፤

ወሰበኩ: ወገብሩ: ሐሰተ: ምትሐተ: ዓይን፣

መትተው: የሠሩት: ጣዖት: የዓይን: ምሳ: ነው፤ ለጊዜው: ደስ: ያሰኛል፤

ወይትአመኖ: ገባሪሁ: ለዝኩ: ዘለሊሁ: ገብሮ፣

የሠራውን: ጣዖቱን: ሠሪው: ያምነዋል፤ አንድም: መልክ: መልካም: የቀና: እንጨት: ያየ: እንደሆነ: ይህ: ጣዖት: ይሆናል: ይላል፤

ከመ: ይግበር: ጣዖተ: በሐመ፣

ቀጥሎ: ቀጥሎ: ጣዖት: ይሠራ: ዘንድ፤

፲፱፤ አሌ: ሎቱ: ዘይብሎ: ለዕፅ: ንቃሕ፣

እኛ: ንቃሕ: እግዚኦ: ለምንት: ትነውም: እንድንል፣ እንጨቱን: ንቃሕ: እግዚኦ: ለሚል: ወዮለት፣

ወተንሥእ፣

እኛ: ተንሥእ: እግዚኦ: እንድንል፣ ጣዖቱን: ተንሥእ: እግዚኦ: ለሚል: ወዮለት፤



ወይብሎ: ለዕብን: ተለዓል፣

እኛ: ተለዓልከ: እግዚኦ: እንድንል፣ ደንጊያውን: ተለዓል: እግዚኦ: ለሚል: ወዮለት፤

ወውእቱኒ: ሐሰት፣

ይኸውም: ሐሰት: ጣዖት: ነው፤

ወይገብርዎ: በወርቅ: ወበብሩር፣

በወርቅ: በብር: ይሠሩታል፣

ወአልቦ: ነፍስ፣

አእምሮ: የለውም፤

፳፤ ወእግዚአብሔርሰ: ውስተ: ጽርሐ: መቅደሱ፣

እግዚአብሔር: ግን: በመመስገኛው: ቦታ: በጽርሐ: አርያም: ይኖራል፤

ወትፈርሆ: ኵላ: ምድር: እምቅድመ: ገጹ፣

ከገጹ: መዓቱ: የተነሣ: ምድር: ሁሉ: ትፈራዋለች።

## ምዕራፍ ፫

ጸሎቱ: ለዕንባቆም: ነቢይ: ምስለ: ስብሐተ: እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔርን: ከመለመንና: ከማመስገን: ጋራ: ዕንባቆም: የተናገረው: ነገር: ይህ: ነው፤

፩፤ ወይቤ: ዘንተ: እግዚኦ: ሰማዕኩ: ድምፀከ: ወፈራህኩ፣

ቀድሞ: ይህን: ዓለም: ካለመኖር: ወደመኖር: አምጥቶ: [illegible] ሰማሁ፤

ዛሬም: ከመኖር: ወደአለመኖር: ስታሳልፈው: አይቼ: ሥራህን: አደነቅሁ፤

፪፤ በማዕከለ: ፪ዔ: እንስሳ: ርእኩከ፣

በጻድቃንና: በኃጥአን: መካከል: አየሁህ:

ከመ: ከመ: ይቀርብ: ዓመቲሁ: አእምረከ፣

የዕለተ: ምጽዓት: ጊዜው: ሳይቀርብ: እንደ: ቀረበ: እንደ: ቀረበ፡አድርጌ፡አውቅሃለሁ፤

ወከመ: ከመ: ይበጽሕ: ጊዜሁ: አሌብወከ፣

የዕለተ: ምጽአት: ጊዜው: ሳይደርስ: እንደደረሰ: እንደደረሰ: አድርጌ: ልብ: አደርግሃለሁ፤

ወሶበሂ: ትትሀወክ: ነፍስየ: እመንሱት: በምሕረትከ: ተዘከረኒ፣

ከኃጥአን: ጥፋት: የተነሣ: ሰውነቴ: በታወከች: ጊዜ: በቸርነትህ: አስበኝ፣ ከጻድቃን: ተደርቦ: እንዲህ: አለ፤ አንድም: እግዚኦ: ሰማዕኩ: ብለህ: መልስ፣ ቀድሞ: ስሳውን: ዕልፍ: አጋር: በምድረ: በዳ: እንደቅጠል: አረገፋቸው፣ እንደ ሻሽ: አነጠፋቸው: ሲሉ: ሰምቼ: ፈራሁ፣ ዛሬም፣ አሥሩን: ነገድ: በስልምናሶር፣ ሁለቱን: ነገድ: በናቡከደነፆር: ስታስማ

www.ethiopianorthodox.org

ርካቸው: አይቼ: ሥራህን: አደ
ነቅሁ፣ በስልምናሶርና: በናቡ
ከደነፆር: መካከል አየሁህ፣ የዕ
ለተ: ዔዋዌ ጊዜው: ሳይቀርብ:
እንደቀረበ: እንደቀረበ: አድርጌ:
አውቅሃለሁ፣ የዕለተ: ዔዋዌ:
ጊዜው: ሳይደርስ: እንደደረሰ:
እንደደረሰ: አድርጌ: ልብ: አደ
ርግሃለሁ፣ ከእስራኤል: ጥፋት:
የተነሣ: ሰውነቱ: በታወከች:
ጊዜ: በቸርነትህ: አስበኝ፣ ከነ
ቢያት: ከካህናት: ተደርቦ: እን
ዲህ: አለ፤ አንድም: ቀድሞ:
ሰብአ: ትካትን: በማየ: አይህ፣
ሰብአ: ሰዶምን: በእሳት: አጠ
ፋቸው: ሲሉ: ሰምቼ: ፈራሁ፣
ዛሬም: የባቢሎንን: ሰዎች:
በቂሮስ: በዳርዮስ: ስታጠፋ
ቸው: አይቼ: ሥራህን: አደነ
ቅሁ፣ በቂሮስና: በዳርዮስ: መካ
ከል: አየሁህ፣ የዕለተ: ሚጠት:
ጊዜው: ሳይቀርብ: እንደቀረበ:
እንደቀረበ: አድርጌ: አውቅሃ
ለሁ፣ የዕለተ: ሚጠት: ጊዜው:
ሳይደርስ: እንደደረሰ: እንደደ
ረሰ: አድርጌ: ልብ: አደርግሃ
ለሁ፣ ከባቢሎን: ሰዎች: ጥፋት:
የተነሣ: ሰውነቴ በታወከች:
ጊዜ: በቸርነትህ አስበኝ፣ ከት
ሩፋን: ተደርቦ: እንዲህ: አለ፣
ነቢይ: ለሁሉ: ያዝናልና፤ አን
ድም: ቀድሞ: ከአብ: ያለ
እናት: ተወለደ: ሲሉ: ሰምቼ:
ፈራሁ፣ ዛሬም: ከእመቤታችን:
ያለ: አባት: ስትወለድ: አይቼ:
አደነቅሁ፣ በኅል: በአህያና:
በላም: መካከል: ተጥለህ: አየ
ሁህ፤ ወአስተማወቅዎ: እስት
ንፋስ: አድግ: ወላህም: እንዲል፣
የዕለተ: ልደት: ጊዜው: ሳይ
ቀርብ: እንደቀረበ: እንደቀረበ:
አድርጌ: አውቅሃለሁ፣ የዕለተ:
ልደት: ጊዜው: ሳይደርስ: እን
ደደረሰ: እንደደረሰ: አድርጌ:
ልብ: አደርግሃለሁ፣ ከአጋንንት:
ድል: ከመነሣት: የተነሣ: ሰው
ነቴ: በታወከች: ጊዜ: በቸርነ
ትህ: አስበኝ፣ ከነፍሳት: ተደርቦ:
እንዲህ: ይላል፤ አንድም: ቀድሞ:
ዲያብሎስን: በጨለማ: አገ
ናጥፎ: እንጦርጦስ: አወረደው:
ሲሉ: ሰምቼ: ፈራሁ፣ ዛሬም:
በመስቀል: ድል: ስትነሣው:
አይቼ: ሥራህን: አደነቅሁ፣
በፈያታዊ ዘየማንና: በፈያ
ታዊ: ዘፀጋም: መካከል: ተሰ
ቅለህ: አየሁህ፤ አንድም: ዮሴ
ፍና ኒቆዲሞስ: በድርብ: በፍታ:
ሲገንዙህ: አየሁህ፣ የዕለተ: ስቅ
ለት: ጊዜው: ሳይቀርብ: እንደ
ቀረበ: እንደቀረበ: አድርጌ: አው
ቅሃለሁ፣ የዕለተ: ስቅለት:
ጊዜው: ሳይደርስ: እንደደረሰ:
እንደደረሰ: አድርጌ: አውቅሐ
ለሁ፣ ከአይሁድ: ጥፋት: የተ
ነሣ: ሰውነቴ: በታወከች: ጊዜ:
በቸርነትህ: አስበኝ፣ ከሐዋር
ያት: ተደርቦ: እንዲህ: አለ



፫፤ እግዚአብሔርሰ: እምቴማን:
ይመጽእ፣
ቴማን: ያላት: ኤዶምያስ: ናት:
እግዚአብሔር: እስራኤልን: ከግ
ብጽ: አውጥቶ: በኤዶምያስ:
አውራጃ: ተአምራቱን: እንደ
አደረገ፣ ትሩፋንን: ከባቢሎን:
አውጥቶ: በኤዶምያስ: አው
ራጃ: ተአምራት: አደረገ፤
ወቅዱስኒ: እምደብረ: ፋራን: ወእም
አህጉረ: ይሁዳ፣
ጽኑ: ክቡር: ልዩ: የሚሆን:
እርሱ: ትሩፋንን: ከባቢሎን:
አውጥቶ: በፋራንና: በይሁዳ:
አውራጃ: ተአምራቱን: ያደር
ጋል፤ አንድም: እንተ: የማን:
ሲል: ነው፣ በሰባ: ዘመን: በየ
ማኑ: ኃይል: ይመጣል፤ አን
ድም: ቴማን: ሰማይ: ነው፤
በአምስት: ሺህ: ከአምስት:
መቶ: ዘመን: ስልብሰተ: ሥጋ:
ይመጣል፤ አንድም: ከአንዱ:
ሀገር: ወደ አንዱ: ሀገር: ሰማ
ስተማር: ይመጣል፤
ወቅዱስኒ: እምደብረ: ፋራን: ወእ
ምአህጉረ: ይሁዳ፣
ጽኑ: ክቡር: የሚሆን: እምደ
ብረ: ፋራን: ወእምአህጉረ: ይሁዳ:
[illegible]
ከተወለደች: ከእመቤታችን:
ይወለዳል፣ ደብረ: ፋራን: ዘሰን
ባቆም: የሚያሰኛት: ይህ: ነው፤
ከደነ: ሰማያተ: ስኑ፣
ሥልጣኑ: ሰማያትን: ፈጠረ፤
ወመልአ: ምድረ: ስብሐቲሁ፣
ሥልጣኑ: ምድርን: ፈጠረ፤
አንድም: በዔዋዌ: የእስራኤልን:
ልዑላኑን: ትሑታኑን: አስማ
ረከ፤ አንድም: በሚጠት: ሥል
ጣኑ: የአሕዛብን: ልዑላኑን:
ትሑታኑን: አስማረከ፤ አን
ድም: መላእክት: አመሰ
ገኑ፣ ኖሎት: አመሰገኑ፤ በዕ
ለተ: ልደት: አንድ: ሁነው:
አመስግነዋልና፤
ዮም: አሐደ: መርዔተ: ኮኑ:
መላእክት: ወሰብእ: ከመ:
ይሰብሕዎ: ለክርስቶስ: በቃለ:
አሚን: እንዲል፤ አንድም:
በሰማይ: ሦስት: ተአምራት:
ተደረገ፣ ፀሐይ: ጨልሟል:
ጨረቃ: ደም: ሁኗል፣ ከዋክብት:
ረግፈዋልና፣ በምድርም:
አራት: ተአምራት: ተደርጓል፣
መቃብራት: ተከፍተዋል፣
ሙታን: ተነሥተዋል፣ አዕ
ባን: ተፈትተዋል፣ መንጦላ

www.ethiopianorthodox.org

ዕተ፡ መቅደስ፡ ተቀድሷልና፤ አንድም፡ ሰማይ፡ ምድር፡ አለፉ፣ ሰማይን፡ አሳለፈ፣ ምድርን፡ አሳለፈ፡ ብትልም፡ ይሆናል፤

፬፤ ወፀዳሉ፡ ከመ፡ ብርሃን፡ ውእቱ፣

ፀዳለ፡ ረድኤቱም፡ ብርሃን፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡ ያሰኛል፤ አንድም፡ ብርሃኑ፡ ወልድ፡ ብርሃን፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡ ያሰኛል፤ አንድም፡ ፀዳልናሁ፡ ሲል፡ ነው፤ ብርሃንነቱ፡ እንደ፡ አብ፡ ብርሃን፡ ነው፤

አቅርንት፡ ውስተ፡ እደዊሁ፡

ስልምናሶር፡ ናቡከደነፆር፡ በእጆቹ፡ ተይዘዋል፤ አንድም፡ በእጆቹ፡ በስልምናሶር፡ በናቡከደነፆር፡ ሥልጣን፡ አለ፤ አንድም፡ ቂሮስ፡ ዳርዮስ፡ በእጆቹ፡ ተይዘዋል፤ አንድም፡ በእጆቹ፡ በቂሮስ፡ በዳርዮስ፡ ሥልጣን፡ አለ፤ አንድም፡ ሄኖክ፡ ኤልያስ፡ በእጆቹ፡ ተይዘዋል፣ በእጆቹ፡ በሄኖክ፡ በኤልያስ፡ ሥልጣን፡ አለ፤ አንድም፡ ሐዋርያት፡ በእጆቹ፡ ተይዘዋል፤ አንድም፡ በእጆቹ፡ በሐዋርያት፡ ሥልጣን፡ አለ፤ አንድም፡ ቅንዋት፡ በእጆቹ፡ ተይዘዋል፤

ወረሰየ፡ ፍቁረ፡ በዕንዓ፡ ኃይሉ፣

በከሃሊነቱ፡ ጽናት፡ የሚወደድ፡ ነገር፡ አደረገ፣ አሥሩን፡ ነገድ፡ አስማርኮ፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ ማዳኑ፤ አንድም፡ አሥሩን ነገድ፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ አስማርኮ፡ ትሩፋንን፡ ማዳኑ፤ አንድም፡ አይሁድን፣ አጋንንትን፣ መናፍቃንን፡ አጥፍቶ፡ ሐዋርያትን፣ ነፍሳትን፡ ማዳኑ፡ ነው፤

፭፤ ወየሐውር፡ ቃል፡ ቅድመ፡ ገጹ፣

በዘሩባቤል፡ በፊቱ፡ ትእምርተ፡ መንግሥት፡ አለ፤ ሳንቲ፡ ዛጉፍ፡ ይነፋል፣ ድብ፡ አንበሳ፡ በፊቱ፡ ይሳባል፤ አንድም፡ በጌታ፡ በፊቱ፡ ዮሐንስ፡ ያስተምራል፣ መንፈቅ፡ በፅንስ፣ መንፈቅ፡ በልደት፣ መንፈቅ፡ በማስተማር፡ ይቀድመዋልና፤

ወይወጽእ፡ ውስተ፡ ገዳም፡ እምድኅረ፡ እገሪሁ፣

ጌታ፡ በስልምናሶር፡ በናቡከደነፆር፡ አድሮ፡ ወደኢየሩሳሌም፡ ይሄዳል፤ አንድም፡ የእስራኤል፡ ንጉሥ፡ የአሕዛብን፡ ንጉሥ፡ ተከትሎ፡ ይሄዳል፣ ማራኪ፡ በፊት፡ ተማራኪ፡ በኋላ፡ ነውና፤ አንድም፡ በእገሪሁ፡ ይላል፣

www.ethiopianorthodox.org



የእስራኤል፡ ንጉሥ፡ በእግሩ፡ ይሄዳል፣ ንጉሥ፡ ነኝና፡ ሠረገላ፡ ይጠረብልኝ፣ ፈረስ፡ ይሳብልኝ፡ አይልም፤ አንድም፡ ጌታ፡ በቂሮስ፡ በዳርዮስ፡ አድሮ፡ ወደባቢሎን፡ ይሄዳል፤ አንድም፡ የባቢሎን፡ ንጉሥ፡ የቂሮስ፡ የዳርዮስን፡ እግር፡ ተከትሎ፡ ይሄዳል፣ ማራኪ፡ በፊት፡ ተማራኪ፡ በኋላ፡ ነውና፤ አንድም፡ በእገሪሁ፡ ይላል፣ የባቢሎን፡ ንጉሥ በእግሩ፡ ይሄዳል፣ ንጉሥ፡ ነኝና፡ ሠረገላ፡ ይጠረብልኝ፣ ፈረስ፡ ይሳብልኝ፡ አይልም፤ አንድም፡ ጌታ፡ ከተጠመቀ፡ በኋላ፡ ወደ ገዳም፡ ይሄዳል፤ አንድም፡ እምድኅረ፡ እገሪሁ፡ ጌታን፡ ተከትለው፡ ምእመናን፡ ወደገዳም፡ ይሄዳሉ፣ ተጠምቆ፡ ወደገዳም፡ መሄዱ፡ ተጠምቃችሁ፡ ወደገዳም፡ ሂዱ፡ ሲል፡ ነውና፤ አንድም፡ በእገሪሁ፡ ጌታ፡ በእግሩ፡ ወደቀራንዮ፡ ይሄዳል፣ ንጉሥ፡ ነኝና፡ ፈረስ፡ ይሳብልኝ፣ ሠረገላ፡ ይጠረብልኝ፡ አይልም፤ አንድም፡ ሰማዕታት፡ እሱን፡ አብነት፡ አድርገው፡ ወደ መስቀል፡ ወደመቸንከር፡ ይሄዳሉ፤

፮፤ ወሶበሂ፡ ይቀውም፡ ታድለቀልቅ፡ ምድር፣

ጌታ፡ በዜዋዌ፡ በግብር፡ መጥቶ፡ በቆመ፡ ጊዜ፡ ኢየሩሳሌም፡ ትነዋወጣለች፤

ወአመሂ፡ ነጸረ፡ ይትመሰዉ፡ አሕዛብ፣

በዓይነ፡ መዓት፡ በተመለከታቸው፡ ጊዜ፡ ሕዝቡ፡ እንደሰም፡ ይቀልጣሉ፤

ወይትቀጠቀጡ፡ አድባር፡ እምኃይሉ፣

ከኃይሉ፡ የተነሣ፡ ነገሥታቱ፡ በመከራ፡ ይንቀጠቀጣሉ፤

ወይትመሰዉ፡ አውግር፡ ዘእምዓለም፣

ከጥንት፡ ጀምሮ፡ የነበሩ፡ መኳንንቱ፡ እንደሰም፡ ይቀልጣሉ፤ አንድም በሚጠት፡ በባቢሎን፡ ወጥቶ፡ በቆመ፡ ጊዜ፡ ባቢሎን፡ ትነዋወጣለች፣ በዓይነ፡ መዓት፡ ባያቸው፡ ጊዜ፡ ሕዝቡ፡ እንደሰም፡ ይቀልጣሉ፣ አድባር፡ ነገሥታቱ፣ አውግር፡ መኳንንቱ፡ ይጠፋሉ፤ አንድም፡ ጌታ፡ በቀራንዮ፡ መጥቶ፡ በቆመ፡ ጊዜ፡ ምድር፡ ትነዋወጣለች፣ በመዓት፡ ባያቸው፡ ጊዜ፡ አይሁድ፡ መናፍቃን፡ ይጠፋሉ፣ እንዲህ፡ እያልህ፡ ውረድ፤ አንድም፡ አሕዛብ፡ ያላቸው፡ ሕዝቡ፡ ናቸው፣ አውግር፡

ሄሮድስ፡ ጲላጦስ፣ አድባር፡ ሐና፡ ቀያፋ፡ እንደሰም፡ ይቀልጣሉ፤ አንድም፡ በደብረ፡ ጽዮን፡ መጥቶ፡ በቆመ፡ ጊዜ፡ ምድር፡ ታልፋለች፣ አይሁድ፡ መናፍቃን፡ ይጠፋሉ፣ ተራራው፡ ኮረብታው፡ ያልፋል፤

ወፍኖቶሂ፡ ዘእምዓለም፡ ርኢኩ፣

ቀድሞ፡ ይህን፡ ዓለም፡ ካለመኖር፡ ወደመኖር፡ አምጥቶ፡ ፈጠረው፡ ሲሉ ሰማሁ፣ ዛሬም፡ ከመኖር፡ ወደአለመኖር፡ ሲያሳልፈው፡ አየሁ፤ አንድም፡ ቀድሞ፡ ስሳውን፡ ዕልፍ፡ አጋር፡ በምድረ፡ በዳ፡ እንደሻሽ፡ አነጠፋቸው፣ እንደ፡ ቅጠል፡ አረገፋቸው፡ ሲሉ፡ ሰማሁ፣ ዛሬም፡ አሥሩን፡ ነገድ፡ በስልምናሶር፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ በናቡከደነፆር፡ ሲያስማርካቸው፡ አየሁ፤ አንድም፡ ቀድሞ፡ ሰብአ፡ ትካትን፡ በማየ፡ አይኅ፡ ሰብአ፡ ሰዶምን፡ በእሳት፡ አጠፋቸው፡ ሲሉ ሰማሁ፣ ዛሬም፡ የባቢሎንን ሰዎች፡ በቂሮስ፡ በዳርዮስ፡ ሲያጠፋቸው፡ አየሁ፤ አንድም፡ ቀድሞ፡ ከአብ፡ እንበለ፡ እም፡ ተወለደ፡ ሲሉ፡ ሰማሁ፣ ዛሬም፡ ከእመቤታችን፡ እንበለ፡ አብ፡ ተወለደ፡ ሲሉ፡ አየሁ፤ አንድም፡ ቀድሞ፡ ዲያብሎስን፡ በጨለማ፡ አጕናጽፎ፡ እንጦርጦስ፡ አወረደው፡ ሲሉ፡ ሰማሁ፣ ዛሬም፡ በመስቀል፡ ድል፡ ስትነሣው፡ አየሁ፤

፯። አዕዋፋት፡ ኢትዮጵያ፡ ይደነግፃ፣

የኢትዮጵያ፡ አውራጃዎች፡ ይደነግጣሉ፤

አዕፃዳቲሆሙ፡ ለብሔረ፡ ምድያም፣

ምድያም፡ ሰማሰት፡ ደግሞ ታል፣ የምድያም፡ አውራጃ፡ ሁሉ፡ ይደነግጣሉ፤

በላዕለ፡ አፍላግስ፡ ኢትመዓዕ፡ እግዚኦ፣

አቤቱ፡ በእስራኤል፡ ነገሥታት፡ ላይ፡ ፊጽመህ፡ አትቆጣ፤

፰። ወኢይከውን፡ መዓትከ፡ በላዕለ፡ አፍላግ፡

መዓትህ፡ በእስራኤል፡ ነገሥታት፡ ላይ፡ አይሁን፤

ወኢመቅሠፍትከ፡ ዲበ፡ ባሕር፣

መቅሠፍትህም፡ በእስራኤል፡ ከተማ፡ ላይ፡ አይሁን፤

እስመ፡ ተዕዕንከ፡ ዲበ፡ አፍራሲከ፣

በፈረሶችህ፡ በስልምናሶር፡ በናቡከደነፆር፡ አድረህ፡ መጥተሃልና፤

አፍራሲከኒ፡ ሕይወት፡ ውእቱ፣

ፈረሶችህ፡ ስልምናሶር፡ ናቡከደነፆር፡ ለነቢያት፡ [illegible]



ሕይወት፡ ናቸው፣ ሕያዋን፡ ቢል፡ እስከ፡ ጊዜያቸው፡ ድረስ፡ ሕያዋን፡ ናቸው፤ አንድም፡ በፈረሶችህ፡ በቂሮስ፡ በዳርዮስ፡ አድረህ፡ መጥተሃልና፣ ፈረሶችህ፡ ቂሮስ፡ ዳርዮስ፡ ለትሩፋን፡ ሕይወት፡ ናቸው፤ ሕያዋን፡ ቢል፡ እስከ፡ ጊዜያቸው፤ አንድም፡ በፈረሶችህ፡ በሐዋርያት፡ አድረህ፡ መጥተሃልና፡ ፈረሶችህ፡ ሐዋርያት፡ መክረው፡ አስተምረው፡ ለሰው፡ ሕይወት፡ ናቸው፣ ሕያዋን፡ ቢል፡ እስከ፡ ጊዜያቸው፤ አንድም፡ በፈረሶችህ፡ በኪሩቤል፡ አድረህ፡ መጥተሃልና፡ ፈረሶችህ፡ ኪሩቤል፡ ለሰው፡ ሕይወት፡ ናቸው፣ ሕያዋን፡ ቢል፡ የተመቸ፡ ነው፤ አንድም፡ በፈረሶችህ፡ በሄኖክ፡ በኤልያስ፡ አድረህ፡ መጥተሃልና፣ ፈረሶችህ፡ ሄኖክ፡ ኤልያስ፡ መክረው፡ አስተምረው፡ ለሰው፡ ሕይወት፡ ናቸው፣ ሕያዋን፡ ቢል፡ እስከ፡ ጊዜያቸው፡ ድረስ፤

፱። ወተርከ፡ ወወሠተ፡ ቀስተከ፡ ዲበ፡ አብትር፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፣

እስራኤል፡ ይሆንልኛል፡ ብለህ፡ በአሕዛብ፡ ላይ፡ ቀሥትህን አዘጋጀህ፣ ሳብክ፤

ፈለግስ፡ ይሰጥቃ፡ ለምድር፣

ነገር፡ ግን አንተ፡ እንዳልህ፡ አይ[illegible] አሕዛብ፡ ከተማህን፡ ይረጋግጠዋል፤ አንድም፡ አሕዛብ፣ ይሆንልኛል፡ ብለህ፡ በእስራኤል፡ ላይ፡ ቀስትህን፡ አዘጋጀህ፣ ሳብህ፣ ነገር፡ ግን፡ አንተ፡ እንዳልህ፡ አይደለም፣ እስራኤል፡ ከተማህን፡ ይረግጠዋል፤ አንድም፡ አሕዛብ፡ ይሆንልኛል፡ ብለህ፡ በሐዋርያት፡ ላይ፡ ቀስትህን፡ ሳብህ፣ አዘጋጀህ፣ ነገር፡ ግን፡ አንተ፡ እንዳልህ፡ አይደለም፣ ሐዋርያት፡ ከተማህን፡ ይረጋግጡታል፡ በነፋስ፡ ይሰቅሏቸዋል፣ በሴጌዎን፡ ይነጹዋቸዋል፡ (ይጥሏቸዋል)፤

፲። ይሬእዩከ፡ ወይዔግሩ፡ አሕዛብ፣

አሕዛብ፡ አንተን፡ አይተው፡ ይጨነቃሉ፤

ወይዘረዉ፡ ከመ፡ ማይ፡ በፍኖት፡

በጕዳና፡ እንደመስና፡ ውሃ፡ ይለያያሉ፣ ከዚህ፡ ውሀ፡ አግኝተን፡ ጠጥተን፡ ነበር፡ እያሉ፣

ወወሀበት፡ ቀላይ፡ ቃላ፣

ቤተ እስራኤል፡ ቃሏን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አድርጋ፡ አመሰገነች፤

ወአልዓለት፡ ግርማሃ፣

መፈራቷን፡ ገለጠች፤

፲፩። ተንሥአ፡ ፀሐይ፡ ወወርኅ፡ ወቆሙ፡ በሥርዓትከ፣

ፀሐይ፡ ጨረቃ፡ ተፈጠሩ፣ በተፈጥሯቸው፡ ጸኑ፤ አንድም፡ ፀሐይ፡ ሲቀ፡ ካህናቱ፣ ወርህ፡ የእስራ

www.ethiopianorthodox.org

ኤል፡ ንጉሡ፡ ተማረኩ፤ በመማረካቸው፡ ጸኑ፤ አንድም፡ ፀሐይ፡ የአሕዛብ፡ ንጉሡ፤ ወርኅ፡ ቢትወደዱ፡ ተማረኩ፤ በመማረካቸው፡ ጸኑ፤ አንድም፡ በዕለተ፡ ዓርብ፡ ፀሐይ፡ ጨረቃ፡ ተለወጡ፤ በዚያው፡ እስከ፡ ሠርክ፡ ጸኑ፤ አንድም፡ ፀሐይ፡ ጨረቃ፡ ያልፋሉ፡ በኅልፍቱ፡ ይጸናሉ፤

በብርሃነ፡ ማዕበልከ፡ የሐውሩ፡

ዓረብ፡ ቃራ፡ ጭሆ፡ በሆነ፡ ሰይፈ፡ ረድኤትህ፡ ጸንተው፡ ይኖራሉ፤

ወበጸዳለ፡ መብረቅ፡ ወልታከ፤

እንደመብረቅ፡ የሚያስፈራ፡ በሆነ፡ ጋሻ፡ ረድኤትህ፡ ጸንተው፡ ይኖራሉ፤

፲፪፤ በመዓትከ፡ ውኅደት፡ ምድር፤

በዜዋዌ፡ ኢየሩሳሌም፤ በሚጠት፡ ባቢሎን፡ ጠፋች፤

ወታፀድፎሙ፡ ለአሕዛብ፡ በመዓትከ፤

በዜዋዌ፡ እስራኤልን፡ በሚጠት፡ አሕዛብን፡ ፈርደህ፡ ታጠፋቸዋለህ፤

፲፫፤ ወወጻእከ፡ ለአድኅኖ፡ ሕዝብከ፤

ወገኖችህ፡ እስራኤልን፡ ለማዳን፡ በረድኤት፡ ወጣህ፤

ከመ፡ ታድኅኖ፡ ለመሲሕከ፤

ቀብተኸ፡ ያነገሥኸው፡ ዘሩባቤልን፡ ታድነው፡ ዘንድ፤ አንድም፡

ወወጻእከ፡ ለአድኅኖ፡ መሲሕከ፤

ቀብተኸ፡ ያነገሥኸውን፡ ዘሩባቤልን፡ ለማዳን፡ ወጣህ፤

ከመ፡ ያድኅኖሙ፡ ለቅቡዓኒከ፤

ነቢያት፡ ካህናትን፡ ያድናቸው፡ ዘንድ፤ አንድም፡ ልጅህን፡ ለማስነሣት፡ ወጣህ፡ ምእመናንን፡ ያድናቸው፡ ዘንድ፤ ድኅኖ፡ አድኃነ፡ ካልዓኒሁ፡ እንዲል፤

ወወደይከ፡ ውስተ፡ አርእስቲሆሙ፡ ለኃጥአን፡ ሞተ፤

በኃጥአን፡ ሞትን፡ አመጣህባቸው፤

ወአንሣዕከ፡ ማዕሠረ፡ ውስተ፡ ክሣውዲሆሙ፡ ለዝሉፉ፤

በአንገታቸው፡ ማሠሪያ፡ አነሣህ፡ ማለት፡ ሞትን፡ አመጣህባቸው፤ የሸህ፡ ፍልጥ፡ ማሠሪያው፡ ልጥ፡ እንዲሉ፤

፲፬፤ ወመተርከ፡ አርእስተ፡ ኃያላን፡ በድንጋፄ፡ ወይትሐወኩ፡ ባቲ፤

በድንጋፄ፡ ተይዘው፡ ሣለ፡ የኃያላኑን፡ ቸብቸቦ፡ ቆረጥህ፤ በዚችም፡ ይታወካሉ፤

ወይከሥቱ፡ አፉሆሙ፡ ከመ፡ ዘይበልዕ፡ ነዳይ፡ በጽሚት፤

ድሀ፡ ውሎ፡ አድሮ፡ እያዋዋጠ፤ ቀስ፡ ቀስ፡ እያለ፡ እንዲበላ፤ ቀስ፡ ቀስ፡ ብለው፡ ብልጣሶር፡ ሞተ፡ ብለው፡ ይናገራሉ፤ አንድም፡ ለድሀ [illegible]



ለት፤ መለከት፡ ይነፋለት፡ አይባልምና፤ ድሀ፡ ቀስ፡ ቀስ፡ ብሎ፡ እንዲበላ፡ ቀስ፡ ቀስ፡ እያሉ፡ ብልጣሶር፡ ሞተ፡ እያሉ፡ ይናገራሉ፤ ታሪክ፡ ይህስ፡ እንደምነው፡ ቢሉ፡ ብልጣሶር፡ ቂሮስ፡ ዳርዮስን፡ በጽንፈ፡ ትዕይንት፡ ድል፡ ነስቶ፡ ሽህ፡ መኳንንት፡ ይዞ፡ በአዳራሹ፡ ተገኝ፤ ሲያበላ፡ ሲያጠጣ፡ ዛሬ እንጂ፡ እስራኤል፡ ከቂሮስ፡ ከዳርዮስ፡ ጋራ፡ ተደርበው፡ ሊወጉህ፡ ነበር፡ አሉት፡ ቢረዱስ፡ ምን፡ ጎድተው፡ ባይረዱስ፡ ምን፡ ጠቅመው፡ ፈጣሪያቸው፡ አያድን፤ አይረዳ፤ አይታደግ፡ ብሎ፡ አያቱ፡ ናቡከደነፆር፡ አክብሮ፡ ያኖረው፡ የነበረውን፡ ንዋየ፡ ቅድሳቱን፡ አምጥቶ፡ በጻሕሉ፡ ፈትፍታችሁ፡ አብሉበት፤ በጽዋው፡ ቀድታችሁ፡ አጠጡበት፡ አለ፤ በጻህሉ፡ ፈትፍተው፡ አበሉበት፡ በጽዋው፡ ቀድተው፡ አጠጡበት፤

ወወጽአት፡ አጽባዕተ፡ እደ፡ ሰብእ፡ ይላል፤ በሰው፡ እጅ፡ አምሳል፡ ስለታየች፡ ነው፡ እንጂ፡ አጽባ[illegible] ናት፤

ወጸሐፈት፡ ቅድመ፡ ኖኅት፡ ኅበ፡ ምረገ፡ ዓረፍት፤

በደጃፉ፡ አንፃር፡ ከግድግዳው፡ ጻፈች፤ አንድም፡ በደጃፉ፡ አንፃር፡ ባለው፡ በዓምዱ፡ ላይ፡ ማኔ፡ ቴቄል፡ ፋሬስ፡ ብላ፡ ጻፈች፤ ንባቡ፡ በዕብራይስጥ፤ ትርጓሜው፡ በሱሩስት፡ ነው፤ ከበላው፡ አብልቶ፤ ከጠጣው፡ አጠጥቶ፡ የሚያኖራቸው፡ ጠቢባን፡ መፈክራን፡ ነበሩት፤ አንብባችሁ፡ ተርጉማችሁ፡ ንገሩኝ፡ አላቸው፤ የማይሆንላቸው፡ ሆነ፤ በዚህ፡ አዝኖ፡ ሳለ፡ የብልጣሶር፡ አያት፡ የኤልማሮዴቅ፡ እናት፡ የናቡከደነፆር፡ ሚስት፡ ናት፤ ዛሬ፡ ልጄ፡ ምሳ፡ አድርጎ፡ ውሎ፡ ነበር፤ ምሳው፡ ቀናለት፡ ይሆን? ብላ፡ ከዳሪ፡ ጠየቀች፤ ምሳውስ፡ ቀንቶለት፡ ነበር፤ ነገር፡ ግን፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ ዓይቶ፡ አዝኗል፡ አሏት፤ ለዚህማ፡ ርእሱ፡ ዘወርቅን፡ ለአባቱ፡ ለናቡከደነፆር፡ የተረጎመለት፡ ዳንኤል፡ ያለ፡ አይደለምን፡ ብላ፡ ሴት፡ ፈጣን (ችኩል) ናትና፡ ልብሷን፡ አንጠልጥላ፡ ገብታ፡ ነገረችው፤ ዳንኤልን፡ አስጠርቶ፡ ይህንን፡ አንብበህ፡ ተርጉመህ፡ ብትነግረኝ፡ የመ

www.ethiopianorthodox.org

ወእትሐሠይ፡ በአምላኪየ፡ ወመድኃኒየ፤

በፈጣሪዬ፡ በመድኃኒቴ፡ አምኜ፡ ደስ፡ ይለኛል፤

፲፱፤ እግዚአብሔር፡ አምላኪየ፡ ወኃይልየ፡ ዘይሠርዖን፡ ለእገርየ፡ ወለ ፍጻሜየ፤

እግሮቼን፡ ፈጽሞ፡ የሚሠራራ ቸው፡ ኃይሌ፡ ፈጣሪዬ፡ እግዚ አብሔር፡ ነው፤

ወያቀውመኒ፡ ውስተ፡ መልዕልት፡

በልዕልናም፡ ያጸናኛል፤

ወዲበ፡ ልዑላት፡ ያጼዕነኒ፤

በኃያላኑ፡ ላይ፡ ያሰለጥነኛል፤ አንድም፡ ከሚጠት፡ በኋላ፡ ድን በር፡ ለይልን፡ እያሉ፡ እየተ ሸከሙ፡ ይወስዱት፡ ነበርና፤

ከመ፡ እማዕ፡ በመኃልይሁ፤

በፍኖቱ፡ ሲል፡ ነው፤ በሕጉ፡ ጸንቼ፡ ጠላቴን፡ ድል፡ እነሳ፡ ዘንድ፡ የሚያሰለጥነኝ፡ እሱ፡ ነው፤

ተፈጸመ፡ ዘዕንባቆም፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ የሃሉ፡ ምስሌነ፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፤

አነሳስቶ፡ ለአስጀመረን፡ አስጀ ምሮ፡ ለአስፈጸመን፡ ለእግዚአ ብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግ ባው፡ አሜን፡ በእውነት፡፡

# ዘሶፎንያስ ነቢይ፤

## መቅድም

ሶፎንያስ፡ ማለት፡ ሰፋኒ፤ ስፉን፡ ማለት፡ ነው፤ አንድም፡ ቀዳሲ፡ ሥሉጥ፡ ማለት፡ ነው፤ ነገዱ፡ ከነገደ፡ ንፍታሌም፡ ነው፤ መነሣቱ፡ በኢዮስያስ፡ ዘመን፡ ነው፤ እናቱ፡ ንህባ፡ ትባላለች፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ኀበ፡ ሶፎንያስ፡ ወልደ፡ ኩስ፡ ወልደ፡ ጎዶልያ፡ አሞራዊ፤

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡ ነው፤ የጎዶልያ፡ ልጅ፡ ከሆነ፡ ከኩስ፡ ልጅ፡ ከሶፎንያስ፡ ዘንድ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ ሰብአ፡ አሞርዮን፡ በጠፉበት፡ ወራት፡ ስለተወለደ፡ አሞራዊ፡ አለ፤

ዘሴዴቅያስ፤

የሴዴቅያስ፡ ወገን፡ ከሚሆን፤

በመዋዕለ፡ ኢዮስያስ፡ ወልደ፡ አሞጽ፡ ንጉሠ፡ ይሁዳ፤

በይሁዳ፡ ንጉሥ፡ በአሞጽ፡ ልጅ፡ በኢዮስያስ፡ ዘመን፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ አርእስት፡ ነው፤ ሠለ ስቱ፡ ምዕት፡ ለመጻሕፍት፡ አር እስት፡ ሲሠጡ፡ አርእስት፡ ሰጥ ተውታል፤ እርሱ፡ ግን፡ ነገሩን፡ ሐሲቀ፡ የሐልቁ፡ ብሎ፡ ያመ ጣዋል፤

፪፤ ሐሲቀ፡ የሐልቁ፡ እምገጸ፡ ምድር፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ደርሶ፡ ያረዳል፤ እግዚአብሔር፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ ፈጽመው፡ ይጠ ፋሉ፡ አለ፤

፫፤ የሐልቁ፡ ሰብእ፡ ወእንስሳ፤

ሰውም፡ ከብቱም፡ ያልቃሉ፤

ወየሐልቁ፡ አዕዋፈ፡ ሰማይ፡ ወዓሣተ፡ ባሕር፤

የሰማይ፡ ወፎች፡ የባሕር፡ አሣ ዎች፡ ይጠፋሉ፤ ድርቅ፡ የማ ያስተባብረው፡ የለምና፤ አንድም፡ መኳንንት፡ መሳፍንት፡ ይጠፋሉ፤

ወይደከሙ፡ ኃጥአን፤

አሥሩ፡ ነገድ፡ በጎዳና፡ ይደ ክማሉ፤

ወእጠፍዖሙ፡ ለአማፅያን፡ እምገጸ፡ ምድር፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ ከምድር፡ አጠፋቸዋለሁ፡ አለ፤

www.ethiopianorthodox.org